**ኢትዮጵያዊነት፡-** *የዜጎች መብት ማስከበሪያ ጉባኤ*

**ETHIOPIAWINNET:** ***COUNCIL FOR THE DEFENSE OF CITIZEN RIGHTS***

[www.ethiopiawin.net](http://www.ethiopiawin.net)

**ECDCR P.O Box 171, East Lansing, MI 48823**

04/01/2019

ለክቡር ዶ/ር ዐቢይ አህመድ
የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር
<u>አዲስ አበባ</u>

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር፤

በመጀመሪያ በዜጎች ከፍተኛ መስዋዕትነት የተገኘው ሰላም እንዲጠበቅ፤ የሕግ የበላይነት እንዲረጋገጥ፤ ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩና የሀገር ግንባታ ግቡን እንዲመታ እየወሰዱ ያሉትን አመራር ሙሉ በሙሉ የምንደግፍ መሆናችንን እንገልፃለን። ጅማሮው ተሳክቶ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በነፃነት፤ በእኩልነትና በፍትህ ላይ የተደላደለ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ባለቤት ሆኖ ሕይወቱን እንዲመራ ባለን አቅም ሁሉ ከመንግሥትና ከመሰል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ጋር ተባብረን እንደምንሠራ ልንገልፅዎ እንወዳለን።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር፤

የሁላችንም ስለሆነችው መዲናችን አዲስ አበባ ላይ አተኩሮ የተነሳው የባለቤትነት ጥያቄ ያስከተለው አላስፈላጊ ውዝግብ ወዴት እንደሚወስደን መገመት አያስቸግርም። ይህንንም አደጋ እግምት ውስጥ በማስገባት፤ የባለቤትነት ጥያቄው መንሥዔ፤ ጥያቄው ጊዜውን ጠብቆ ሊነሳ የሚችል ጉዳይ መሆኑና፤ አግባብነቱንም በሚገባ ያጤነ መሆን ነበረበት ብለን እናምናለን። በእኛ አረዳድ የመዲናችንን የባለቤትነትም ሆነ፣ የአስተዳደር፣ የሕዝብ መደራጀትና የማደራጀት መብቶች ሁሉ አሁን በሥራ ላይ ባለው ሕገ መንግሥት በግልጽ ተጠቅሶ የተቀመጠ ስለሆነ ወደ ውዝግብ ሊያመራ አይገባም እንላለን።

ከዚሁ የአዲስ አበባ ባለቤትነት ጥያቄ ጋር ተያያዥነት ያለው በቅርቡ በታዋቂው ጋዜጠኛና የሰብዓዊ መብት ተሟጋች እስክንድር ነጋ መሪነት የተጀመረው የአዲስ አበባ ሕዝብ ሠላማዊ የሆነ የመደራጀት እንቅስቃሴን ተከትሎ በከተማው ባለሥልጣናትና ራሱን የባለ አደራ ምክር ቤት ብሎ በሠየመው ድርጅት መካከል አለመግባባቶች እንደተከሰቱ ታዝበናል። ። በእኛ እምነት፣ የአለመግባባቱ መንስዔ "ባለ አደራና" "ምክር ቤት" የሚለው የንቅናቄው ስያሜ አሻሚና በመንግስትም ቀደም ሲል ተቋቁመው ከሚገኙ መንግሥታዊ ድርጅቶች ጋር መመሳሰሉ ለተከሰተው አለመግባባት አስተዋጽኦ አድርጎ ይሆናል ብለን እናስባለን ። ይህም የአጋጣሚ ስም ተመሳሳይነት በሥራ ድርሻ ተሻሚነት በመተርጎሙ ወደ ተከሰተው አለመግባባት ከመቸኮል በውይይት እንዲፈታ ማድረግ ይቻል ነበር። እስክንድር ነጋ ሀገር ወዳድና በሕይወት ተመክሮው፣ ሥነ

ምግባርና ትሕትና የተመላበት ባህርይ ያለው ሌላ እኩይ አካል ፈጥሮ የአዲስ አበባን ሕዝብ ለሥርዓት አልበኝነት ንቅናቄ አጋልጦ ማየት ይከጅላል ብለን አናምንም። እስክንድርን ከለውጡ መንፈስና አካሄድ ውጭ እንደሆነ ተደርጎ በመፈረጅ ግለሰቡን ማሸማቀቅና፣ ብሎም አላስፈላጊ ዛቻና ማስፈራሪያ ማድረግ ተገቢ አይደለም። ይህን ያደረጉ ወገኖች ቢያንስ መመከር አለባቸው። ከሁሉም በላይ እንዲህ ያለ ድርጊት የሃሳብ ልዩነትን ያሰፋል እንጂ አያጠብም።

ባለ አደራ ምክር ቤት በተሰኘው ስብሰብ በወለደው አለመግባባት በእስክንድር ነጋ ላይ የተሰነዘረው ኃይለ ቃል ሲያሳዝነን፤ በተጨማሪ በዛሬው ዕለት በራስ ሆቴል የተጠራው ሕጋዊ የንቅናቄው ጋዜጣዊ ጉባኤ ከበላይ አካል ተልከን ነው በሚሉ የፖሊስ ሃይል መበተኑ አግባብነት የጎደለው ነው እንላለን ። በአንድ በኩል፤ በተሰብሳቢዎች ላይ በአገኘነው መረጃ መሠረት ከአደጋ ለመጠበቅ ነው ስብሰባውን እንዳይካሄድ ያደረግነው ሲሉ፤ በሌላ ዜና ደግሞ ስብሰባውን በቤተ መንግሥት ከአደጋ ተጠብቀው ማካሄድ እንደሚቻል ሰምተናል። ስብሰባው እንዲቀጥል መፈቀዱና አለመግባባቱንም በውይይት ለመፍታት የሚደረገውን ጥረት እያደነቅን በዘለቄታ የመሰብሰብ፤ በነጻነት የመናገርና ሃሣብን የመግለጽ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ተከብረው ዜጎች ያለምንም እገዳ በመረጡት የመሰብሰቢያ ቦታ የመሰብሰብ መብታቸው እንዲከበር በትህትና እናሳስባለን።

እንደሚታወቀው አዲስ አበባ የፌደራል ቀጠና/ዲስትሪክት ናት። አስተዳደሩም የሚዋቀረው ሕዝብ በሚመርጠው ምክር ቤትና ምክር ቤቱ በሚመርጠው ከንቲባ ነው። የአጎራባች ኦሮሚያን ክልል "ልዩ ጥቅም" በሚመለከት የሕገ መንግሥቱ ጥቅል አቀራረብ ችግር እንዳለ ሆኖ ለሚነሱ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ብክለት ይዘት ያላቸውን ጥያቄዎች ሕዝቡንና ኤክስፐርቶችን ያሳተፈ ጥናት አካሂዶ መመለስ ይቻላል። አስተዳደርና ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸውን ግን ለጊዜው አሳድሮ ሕገ መንግሥቱ እስኪሻሻል መጠበቅ ወይም በአዲስ አበባም ሆነ አጎራባች ወረዳዎች በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት በህዝብ የተመረጡ ተወካዮችን በፍትሃዊ ድርድር መምረጥ ውጤቱን ዘላቂ ያደርጋል።

እውነት ነው ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደገለፁት ሕግ መከበር አለበት። ተቃዋሚም ሆኑ የመብት ተሟጋቾች ለሕግ መገዛት አለባቸው። ሕግ ካልተከበረ ሥርዓት አልበኝነት ይነግሳል። በዚህ በኩል የሚነሳውን የመንግስት ችግር እንረዳለን። ጉዳዩ የሚመለከተው ሁሉ የመንግሥትን የሕግ አስከባሪነት ሃላፊነት ይረዳሉ ብለን እናምናለን።

በአዲስ አበባ ጉዳይ የተነሳው አላስፈላጊ ንትርክ በቀላሉ በውይይት የሚፈታ ነው። አስፈላጊው ነገር ቅንነት ነው። በኛ እምነት የመንግስትም ሆነ የንቅናቄው አመራር አባላት ዲሞክራሲ እንዲጎለብት የሚሞኙ ናቸው። መደራጀት ለውጡ ካመጣቸው ፀጋወች አንዱ መሆኑ ታውቆ መንግስት ምሳሌነቱን በበጎ መልኩ ቢመለከት የፖለቲካውን አውድ ለማረጋጋት ይጠቅማል ብለን እናምናለን።

ስለዚህም የባልደራሱ የሕዝብ አደራጅ አመራር ላይ ከአንዳንድ ወገኖች የተሳሳተ ተርጉም ስልተሰጠው በመሪው ላይና በሕዝቡ ላይ የሚደርሰውን ዛቻና ማስፈራራት እንዲቆም ክቡርነትዎ ምክርና ተግሳጽ

እንዲሰጡና እንደዚህ ያለው የሙብት ጥያቄ ከለውጡ መንፈስ ውጭ እንዳልሆነ ታውቆ ውይይት እንዲጀመር ባክብሮት እንጠይቃለን። ይህንንም እንደሚያደርጉ ሙሉ ተስፋ ነን።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

ዕርቁ ይመር (ዶክተር)
**ሊቀ መንበር፤ ኢትዮጵያዊነት የዜጎች ሙብት ማስከበርያ ጉባዔ**